# አዬ! ኢትዮጵያ: እውነትም "ያልታደልሽ"

ከብርሃኑ ተሰማ

እኔና ጓደኛዬ ምርጫ 1997 የኢትዮጵያን ምርጫ በጥማና ሲንከታተልና በተከታዩ ያስከተልው የመንግስት አደባባይ ግዲያ በማዘን ያልታደለች አገር በማለት አሳዝኖን ቆየ።

መቼም በሕብረተሰብ ታሪክ ውስጥ በሥራችን የፈቀድነውን የመምረጥ ንቃት አለን። አንድ በተሰጠ ጊዜ ውስጥ ይህንን ምርጫ ለማድረግ የሚንችለው ይህ ሥራ ትክክል ነው ያኛው ስህተት ብለን ጉዳዮችን መመርመር ስንችል ነው። ከዚህ እምነት ውጭ ድርጊታችንን ወደ የነቃ ንድፍ ልንለውጠው አንችልም። እነኝህ እምነቶች  ለምንኖርበት፣ ለምንገለፅበት ፋይዳ የጥረታችን አመልካቾች ናቸው።  ይህ መጨረሻና ፋይዳ ለሕይወት ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን ከዚህ ውጪ ግን የተዛባ ሰብዓውነት እናሳድጋለን።

ለጋራ ሥራ የጋራ ውሳኔ/ውይይት/ የመጀመሪያው ሲሆን ይህም ሕይወት ካላገኘ ባዶ ወሬ ብቻ ሆኖ ይቀራል። አባላት ስለድርጅታቸው ዓላማና ደንብ ጠንቅቀው መረዳት መቻል፣ የአመራር አባላት ሥራ መሳካት ዋንኛው ገፅታ ሲሆን እውነተኛ አባል ማለት ደግሞ ያለበትን ድርጅት ጠንቅቆ ሲረዳ በመሆኑ ለዚህም መቀስቀስ ስለአለበት ነው። አመረር አባላት ከጠቅላላው አባላት አንድ እርምጃ ልቀው መገኘት አለባቸው። እንደዚህ ሲሆን ብቻ ነው የአዲስ አባላትን ስነልቦናዊ ዘየ አጥንተው ወደ አባልነት ሊያመጡ የሚችሉት።

እንግድህ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት እነዚህ ሁኔታዎች የሚሟሉት በዲሞክራሲ፣ ሕዝቡ ሥልጣኑን እንዲወስንበት ተደርጎ እንጂ ግለሰቦች በሚፈጥሩት አሻጥርና ደባ አይደለም። ዲማክራሲን አጠር ባለ መልኩ ስንመለከተው የሕብረተስብን ተሳትፎ፣ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት፣ የሕግ የበላይነት፣ የሕዝቡ ነፃ የፖለቲካ ሕይወት፣ የሃሳብ ነፃነትና ባጠቃልይ የአብላጭ አስተዳደርና ለአናሳ ተከላካይ ነው።

ታዲያ የኛዎቹ (ኢትዮጵያዊያን) በተለይ አዲሱ ትውልድ ለዚህ መቆም ሲገባው ለምን አንዳንድ ሰንካላ አስተሳሰብ በመበከል ትግሉ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ መጨመር እንደመረጡ አይገባኝም። በአሁኑ ወቅት የቅንጅት ሁኔታ ትግሉን በሚጎዳ ሂደት ላይ በሚገኝበት ወቅት የችግሩ መንሳዔ ምንድነው በማለት ከመሰረቱ መርምሮ መፍትሄ እንደመሻት በተቃራኒው ቡድን በመፍጠር ችግሩ እንዲባባስ ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል። መሪዎች ሲሳሳቱ እንደመውቀስ ስህተቱን በመደገፍ ለበለጠ ስህተት መንገድ እያሳመረ ቀጥሏል። መሪዎቹ ሲሳሳቱ ተሳስተናል አይሉም። ታዲያ መፍትሄ እንዴት ይገኝ ይሆን!!

በጣም ካሳዘኑኝ ሁኔታዎች፣ ስህተት መፍጠሩ ሳይሆን የተሰራውን ስህተት መካድ ነው። እስቲ የተቀዳሚ ም/ፕሬዝዳንቷ የወ/ሪት ብርቱካን በተለያዩ ወቅቶች ባደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ቃለ ምልልስ ጥቂቱን እንመልከት:

በዳላሱ ሕዝባዊ ስብሰባ፡

ከእስር ቤት ከተለቀቃችሁ በኋላ ታደርጉዋቸው በነበሩት ስብሰባዎች ለምን ያልታሰሩትን የምክር ቤት አባላትን ከስብሰባው አገዳችሁ? ተብሎ ለተጠየቀ ጥያቄ እንደሚከተለው መልሰዋል።

*“እዚህ እስር ቤት ውስጥ ሆነን ሁሉም ውሳኔ አገኙ የተባሉ ለምሳሌ የኪስ (K/C) የኪል (K/L) ጥያቄ የመጀመሪያ ውሳኔ የተሰጠበትና ያን ውሳኔ የስጠው የእስር ቤቱ አካል ነው ጭብቶቹን፣ መነሻዎቹን፣ አላማዎቹን የሚያውቀው።*

*ሌላ ውሳኔ ያልሰጠውን ወገን ጠርቶ ይህንን በተመለከተ ቀጣይነት ምን ትላለህ ማለት ምክንያታዊም አይደለም፣ አግባብም የለውም። ከዚያም በተጨማሪ ከእስር ቤት ከወጣን ተነጋግረንበት ለሕዝብም ለሚመለከታቸውም ወገኖችም መግለጫ የተሰጠንበት ስለእስረኞች ጉዳይ ብቻ በሚመለከት ጥያቄ ነበር። ከእስር አወጣጥን ጉዳይ ቅድም ዶ/ር ብርሃኑ እንደገለፀው……. አንድ ነገር ማድረግ ስለአለብን ስብስባውን በዚያ ነው የጀመርነው።*

*እዚህ እዚህ ጥያቄ ላይ እንበልና ያልታሰሩት ወገኖች አሳትፈናቸው ቢሆን ኖሮ ምን ዓይነት አስተዋኦ የሚኖራቸው? ሂደቱን አያውቁት፡ 18 ወር ሙሉ ከሸማግሌዎች ጋር ሲንነጋገርበት የቆየነው ጉዳይ ነው። ሂደቱን ይዘቱን አጠቃላይ የስምምነቱን መንፈስ የምናውቀው እስር ቤት የነበርን የምክር ቤቱ አባላት ነንና በማያውቁት ነገር ጠርቶ ውስኔ እንዲሰጡ ፤ ውሳኔው በከፍል ተስጥቶ እንደገና ቀጣይነት በተመለከተ ማብራሪያ ወይም ውሳኔ የሚጠይቅ ነገር ላይ እነሱን ማካተት አግባብነት የለውም።”*

በመሰርቱ ወ/ሪት ብርቱካን ምን መብት አላቸው “ሌላ ውሳኔ ያልሰጠውን ወገን ጠርቶ ይህንን በተመለከተ ቀጣይነት ምን ትላለህ ማለት ምክንያታዊም አይደለም፣ አግባብም የለውም።” ብሎ ለመናገር? እውነት የዲማክራሲ ጉዳይ ከሆነ: ማንም የምክር ቤቱ አባላት ፓርላማ የገቡትን ጨምሮ የመገኘት መብት አላቸው። ጉዳዮን አያውቁም ተብሎ ከስብሰባው ማገድ በተቃራኒው ኢ-ዲሞክራሲ ነው የሚሆነው። የአጀንዳውን መሰረት አስቀድሞ የማብራራትና እንዲረዱ የማድረግ የሰብሳቢው ኃላፊነትና ግዴታ ነው። ያውም የምክር ቤት አባላትን የሚያህል በሰፊው ሕዝብ የተመረጡትን (ዲማክራሲ ከሌለ በስተቀር) ማንም ማገድ አይችልም።

በሌላ በኩል ከቪኦኤ ጋዜጠኛ አዲሱ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ለዚሁ ተመሳሳይ ጥያቄ

እንደሚከተለው ተናግራዋል:

*“…የት የት እንዳሉ እንኳን የምክር ቤት አባላቶቻችን ላይ የት እንዳሉ፤ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ለማጣራት ከባድ ሁኔታ ውስጥ ነበር የወደቅነው፤ የሂደቱን ሙሉ ገፅታም ለማሳየት አንዳንድ ከምክር ቤት አባሎቻችን ሁሉም የምክር ቤት አባላት መጠራት የለባቸውም። አንዳንዶቹም ፓርቲውን የሚጎዳ ተግባር ሁላ ላይ ተሰማርተውም ሊሆን ይችላል። ብለው ክርክር አንስተው ብዙ ቀናት የፈጀ ጉዳዩን የሚያጓትት… ከብዙ ሂደት በኋላ በመጨረሻ ሌሎችን ጉዳዮቻችን ተሟልተን ቶሎ ተሟልተን መወሰን ስለአለብን የምክር ብት አባላት በሙሉ እንዲጠሩ ውሳኔ ላይ ደርሶ ጥሪ ተደርጎ የተወሰኑ መምጣት የቻሉ መጥተው የመጀመሪያ ስብሰባ ተደርጎ ነው ወደዚህ መምጣት የቻልነው…”*

እንግዲህ ወ/ሪት ብርቱካን አንዴ የት የት እንዳሉ ለማወቅ ችግር እንደገጠማቸው ሲናገሩ በሌላ አከባቢ ደግሞ ሂደቱን ለማያውቁ ቀጣይነት ምን ትላለህ ማለት ምክንያታዊም አይደለም፣ አግባብነት የለውም፤ ሲሉ ምን ለማለት እንድደሆነ አይገባኝም። ይኸው አሁን በየቦታው ማንም ማንን የመሻር መብት የለውም እያሉ ሲናገሩ፣ ለምን ይሆን እስር ቤት ያልገቡ የፓርቲው ምክር ቤት አባላት የተወገዱት? ደግሞም የት እንዳሉ ለማወቅ ችግር ገጠመን ሲሉ፤ ተመራጮቹ መኖሪያ አልባ (Homeless) ነበሩን? በመቀጠልም ምክንያት ሲስጡ አንዳንድ አባላት ፓርቲውን በሚጎዳ ሥራ ላይ ተስማርተው ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል። የታሰሩትስ ፓርቲውን በሚጎዳ ሥራ ላይ ሊሰማሩ አይችሉም ማን አለ? ቢሆንም ሁሉንም አቅርቦ በመወያየት ጥርጣሬውን ማስወገድ ሲቻል በአሉባልታና ወገናዊነት ላይ በተመሰረተ ሽኩቻ መከፋፈል በአንድ ድርጅት ወስጥ ትልቅ ወንጀል መሆን አለበት።

ወ/ሪት ብርቱካን "ያልታሰሩት ለምን ከስብሰባ ተወገዱ" ለሚለው ጥያቄ ላይ ብዙ አወዛጋቢ መልስ መልሰዋል። ከላይ እንደታየው በቪኦኤው ቃለ ምልልስ *"የምክር ቤት አባላት በሙሉ እንዲጠሩ ውሳኔ ላይ ደርሶ ጥሪ ተደርጎ የተወሰኑ መምጣት የቻሉ መጥተው የመጀመሪያ ስብሰባ ተደርጎ ነው ወደዚህ መምጣት የቻልነው።"* ብለዋል። እንዴ! በተለያየ ቦታና ጊዜ የት እንዳሉ መታወቅ አልተቻለም እየተባለ፤ ፓርቲውን በሚጎዳ ተግባር ላይ ተሰማርተው ሊሆን ይችላል ተብሎ እየተጠረጠሩ፤ ያልታሰሩት በማያውቁት አጀንዳ ላይ ማወያየት አግባብንት የለውም ተብሎ ከስብሰባ እየተወገዱ፤ "መምጣት የቻሉ መጥተው የመጀመሪያ ስብሰባ ተደርጎ" ተወክለን ወደዚህ መጣን ብለው መናገራችው አስዝኖኛል።

በቃለ ምልልሱ በተደጋጋም "ውይይቱ ቀናትን የፈጀ ጉዳዩን የሚያንትት" ብለውም ተናግረዋል። ለመሆኑ እንደዚህ ቀናትን የፈጀ ውይይት ምን መፍትሄ አገኘ? ውይይቱስ አገርን በሚጠቅም ፖሊሲዎች ላይ የተመሰረተ ነበር ወይስ ውጭ የመሄድ ውሳኔን አንተተ? በተለያየ ወቅት ወ/ሪት ብርቱካንና ዶ/ር ብርሃኑ በየአከባቢው የሚያደርጉትን ሕዝባዊ ስብሰባ ውጤት አገር ቤት ሲመለሱ ሪፖርት ለምክር ቤቱ እንደሚያቀርቡ ተናግረዋል። ለየትኛው ምክር ቤት እንደሆነ ግን ግልፅ አይደለም። ከእስር ቤት ለወጡት አባላት ብቻ ከልሆነ፤ ያልታሰሩት (ወ/ሪት ብርቱካን እንዳሉት) በማያውቁት ነገር ላይ እንሱን ማሳተፍ አግባብነት ስለሌለው ድርጅቱ እንዴት ወደፊት እንደሚገፋ ለነሱ ትቻለሁ።

የዚህ ሁሉ ችግሮች በርካታ ቢሆኑም አንደኛው የልምድ እጥረት ነው።፡በሰለጠኑት አገሮች የፓርላማ ሕግ እንኳን አዲስ ተመራጭ የምክር ቤት አባላት (junior parliamentarians) የንዑስ ኮሚቴ መሪነት ቦታ እንኳን ሊይዙ አይችሉም። ለመሪነት የሚያበቃው የሰውነት አቋም ሳይሆን ልምድ በትኛውም ቦታ አስፈላጊነት አልው። በዚህን ወቅት ወ/ሪት ብርቱካን የመምራት ልምድ ስለሌላቸው ልምዱን ቢያጎለብቱ ወደፊት ጥሩ መሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገንዝበውና ለዚህ ትኩረት ሰጥተው በአሁኑ ጊዜ ግን ድርጅቱን በሚጎዳ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ባይገቡ ይመረጣል። አገርን መምራት ቀላል አይደለም። ከቡድን አስተሳሰብ መፅዳት ያስበልጋል። ከወገናዊነት ስሜት በመራቅ ሁሉን ማስተባበር ይኖርበታል። ከሚያሻማና ተቃራኒ መልዕክቶች መቆጠብም በሳልነት ይሆናል።